# የአስር ቀን የአየር ሁኔታና ወርሃዊ

# የአየር ጠባይ

# ግምገማ ትንበያ መጽሔት

## ከዲሴምበር 1-31 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

## እንዲሁም ከጃንዋሪ 1-31/2025

## የሚኖረው ወርሃዊ የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጃንዋሪ 2025

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ


እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ............ - 3 -

ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ............ - 4 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ............ - 6 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምብር 1 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ............ - 6 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምብር 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ............ - 6 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 7 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ............ - 7 -

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ .- 8 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ............ - 8 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ ............ - 9 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ............ - 9 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ............ - 9 -




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በዲሴምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል፡፡ በተለይም በሁለተኛዉ እና በሶስተኛዉ አስር ቀናት የሰሜን ምሥራቅ፣ የመካከለኛው፣ የምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተዘወትሮባቸዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የለሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ጨምሮ የተስተዋለ ሲሆንና በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቅዝቃዜው መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሸየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነትም በአዴት 4.2 3.2፤ አዲግራት 4.5፣ 4፣ 4፣ 4፣ 4፣ 4፣ 4፣ 4፣ 3.5፤ አይደር 4.8፣ 3.8፤ ሐሮማያ 4.4፣ 3.4፣ 2፣ 0.4 1፣ 0.8 1.8፣ 2፣ 1.8፣ 0.2፣ 2 .2፣ 3.8፣ 4.8፣ 4.4፣ 4.6፣ 2.0፣ 1.8፣ 2.0፣ 2.8፣ 0.2፣ 2 .2፣ 3.8፣ 4.8፣ 4.4፣ 4.6፣ 2.0፣ 1.8፣ 2.0፣ 2.8፣ 4.2 ፤ አለም ከተማ 4.8፣ 4.2፣ 4፣ 4.2፣ 4፣ 3.8፣ 3.2፣ 4፣ 3.0፣ 4.2፣ 3.0፣ 4.2፣ 3.2፤ አምባ ማሪያም 3.6፣ 4፣ 3.6፣ 4.2፣ 4፣ 4.5፣ 4.5፣ 3.5፣ 4፣ 4.5፣ 4.5፣ 4.4፣ 4.2፣ 4.0፣ 3.8፣ 4.5፣4.5፣ 4.5፣ 4.4፣ 4.2፣ 4.0፣ 3.8፣ 4.5፣ 4.5፤አርሲ ሮቤ 4፣ 3.5፣ 3.0፣ 3.5፣ 3.5፣ 2.5፣ 3.0፣ 3.5፣ 3.0፣ 3.5፣ 3.5፣ 2.5፣ 3.0፣ 3.0፤ ባህር ዳር 4.6፣ ባቲ 4.8፣ 4፣ 4.2፣ 4.0፣ 3.8፣ 4.2፣4.0፣ 3.8፣ 4.2፤ቡኢ 4፣ 3፣ 4፣ 3፣ 3.6፣ 2፣ 2.5፣ 2.4፣ 3.6፣ 3.6፣ 4.4፣ 4.2፣ 4.0፣ 3.0፣ 2.0፣ 1.0፣ 3.6፣ 3.6፣ 4.4፣ 4.2፣ 4.0፣ 3.0፣ 2.0፣ 1.0፣ 2.4፤ ኮምቦልቻ 3.2 ፣3.2 ፤ደብረ ብርሀን 2.2፣ 2፣ 0.2 0፣ -1.0፣ -1.6፣ -1.4፣ -0.2፣ 1.8፣ 2.4፣ 4.2፣ 2.2፣ -1.0፣ 4.0፣2.4፣ 4.2፣ 2.2፣ -1.0፣ 4.0፣ -2.8፤ደብር ታቦር 2.5፤ዳንግላ 2.5፣ 2፣ 4.5፣ 3.8፣ 4.5፣ 4.5፣ 3.8፣ 4.5፣ 4.5፣ 4.0 ፤ደባርቅ 4.5፣ 3.5፣ 3.5፣ 4፣ 4.6፣ 4.5፣ 4.5፣ 4.6፣ 4.5፣ 4.5፣ 3.5 ፤ደብረ ማርቆስ 2፣ ፤ደብረ ወርቅ 3.2፣ 2፣ 4፣ 4.2፣ 4.2፣4.2፣ 4.2፣ 4.2 ፤ቢሾፍቱ 4.2፣ 4.2፣ 4.4፣ 3.8፣ 2.2፣ 3.1፣ 4.2፣ 4.2፣ 4.1፣ 2.0፣ 4.0፣ 4.2፣ 4.2፣ 4.1፣ 2.0፣ 4.0፣ 2.0፤ ደምቢ ዶሎ 2.8፤እነዋሪ 4.5፣ 2፣ 4.5፣ 4.5፣ 2.6፣ 3.5፣ 3.6፣ 4.0፣ 4.5፣4.0፣ 4.5፣ 4.0፤ በእምድብር 4.8፣ 3.8፣ 4.8፣ 3.8፣ 4.1 ፤ ፍቼ 3.8፣ 3.2፣ 4.2፣ 4፣ 4፣ 3.5፣ 3.5 ፣3.5፣ 3.5፣ 3.0፤ ጉንዶ መስቀል 4.8፣ 4.3፣ 4.8፣ 4.3፣ 4.4፤ ጃራ 4.0፣ 4.0፤ጅግጅጋ 2፣ 2፣ 4.5፣ 4.6፣ 1.4፣ 1.2፣ 1.6፣ 1.2፣ 3፣ 1.8፣2.4፣ 2.4፣ 3.4፣ 3.0፣ 3.2፣ 4.0፣ 0.2፣ 1.0፣ 2.4፣ 2.4፣ 3.4፣ 3.0፣ 3.2፣ 4.0፣ 0.2፣ 1.0 ፤ጅማ 4፣ 2.8፣ 4፣ 4.8፣ 3.2፣ 4.8፣ 3.2፣ 1.4፤በማይጨዉ 4.5፣ 4.0፤ 4.8፣ 4.5፣ 4.0፤ 4.8፣ 3.5፤ መሓል ሜዳ 1፣ 3.2፣ 2.5፣ 2.8፣ 0.2፣ 4.2፣ 4፣ 3፣ 2.5፣ 4.8፣ 3.0፣ 2.6፣ 4.5፣ 0.5፣ 1.2፣ 4.8፣ 3.0፣ 2.6፣ 4.5፣ 0.5፣ 1.2፣ -2.0፤



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሞጣ 4.4 ፤ንፋስ መዉጪያ 4.5፣4.5፤ ሮቤ 4.9፣ 4.6፣ 4.2፣ 3.4፣ 4.6፣ 4.2፣ 3.4፣ 3.8፣ 4.4፣ 3.8፣ 4.4፤ሾላ ገበያ 2.1፣ 1.0፣ 2.1፣ 2.0፣ 1.0፣ 2.0፣ 3.0፣ 2.0፣ 1.0፣ 2.0፣ 1.2፣ 3.0፣ 4.0፣ 3.0፣ 3.3፣ 3.0. 2.1፣ 2.0፣ 2.0፣ 1.2፣ 3.0፣ 4.0፣ 3.0፣ 3.3፣ 3.0. 2.1፣ 2.0፣ 1.1፤ወግል ጤና

4.5፣ 2.5፣ 3፣ 1.5፣ 1፣ 4.5፣ 2.5፣ 4.5፣ 4.2፣ 4.6፣ 2.0፣ 1.8፣ 0.6፣ 4.5፣ 4.2፣ 4.6፣ 2.0፣ 1.8፣ 0.6፣ 0.4 ፤ወረይሉ 4.5 4.5፣ 4.2 ፤እንዲሁም የትኖራ 4 በዲግሪ ሴልሸየስ መመዝገቡን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል (ምስል 1) ፡፡

በሌላ በኩል በጥቂት የደቡብ ምዕራብና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናት ከነበረዉ የደመና ሽፋን ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል። ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በማሻ 64.2፣ 50.4፤ በሮቤ 36፤ በጅንካ 26.2፣ በሳዉላ 22.6፣ በሰመራ 20.2፣ በጎሬ 15.5፤ እንዲሁም በጋቲራ 17.3፣13.8፣ 11.4፤ በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡




**ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ**



ስልክ+2511155383944ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፈዉ የዲሴምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በማሻ፣ በሮቤ፣ በጅንካ፣ በሳዉላ፣ በሰመራ፣ በጎሬ፣ በጋቲራ፣ በተርጫ፣ በጭራ፣ እንዲሁም በፉኙዶ ላይ እስከ 12.6 እስከ 119.4 ሚሜ የሚደርስ ከ3-7 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ እንዲሁም አብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍል በደረቃማው የአየር ሁኔታ ስር ቆይተዋል፡፡ ባለፈዉ አንድ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በጥቂት የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ካርታ 3) ፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምብር 1 እስከ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምብር 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የዲሴምበር ወር በተለይም በመጀመሪያዉና በሁለተኛዉ አስር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የተስተዋለው የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የደረሱ ሰብሎች እንዲደርቁ፣ በጊዜ እንዲሰበሰቡና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን ምቹ ሁኔታ ነበረዉ፡፡ በሌላ መልኩ በአንዳንድ የሰሜን፣ የመካከለኛዉና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን የተነሳ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ሲመዘገብ በተወሰኑ ጥቂት ቦታዎች ላይ ደግሞ ከዜሮ ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም የተስተዋለው ቅዝቃዜ በተለይም በአነስተኛ የቤት  እንስሳት ጤናና፣ በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ የፍራፍሬ ተክሎችና በጓሮ አትክልቶች ላይ በጥቂት ቦታዎች ላይ በተወሰነ መጠን አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ ይሁንና በተለይም በዲሴምበር የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት አልፎ አልፎ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉና በደቡብ ምስራቅ በሚገኙ ጥቂት ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከሞላጎደል ቀጥሎ ተስተዉሏል፡፡ ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ከሰብል ስብሰባ በኋላ ለሚዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎችም ሆነ ለእንስሳት የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ላይ የተገኘው እርጥበት ጠቀሜታ ነበረው(ካርታ 4)፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024

ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ዲሰምበር ወር በአብዛኛው ተፋሰሶች ላይ ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ያመዘነ ሲሆን፤ በአንጻሩ ግን ጥቂት የላይኛዉ እና የመካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ በመካከለኛ ኦሞ ጊቤ እና ስምጥ ሸለቆ ኪስ ቦታዎች እንዲሁም በጥቂት የላይኛው በዋቤ ሸበሌ እና ገናሌ ዳዋ አዋሳኝ ቦታዎች መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ የተቀሩት አብዛኛዎቹ የአባይ፣ የተከዜ፣ የመረብ ጋሽ፣ የአፋር ደናክል፣ የአይሻ፣ የአዋሽ፣ የገናሌ ዳዋ፣ የስምጥ ሸለቆ፣ የኦሞ ጊቤ እና የባሮ አኮቦ ተፋሰሶች በደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ

በሚቀጥለው የጃንዋሪ ወር በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ጠባይ ይስተዋላል፡፡ በሌላ በኩል ከወሩ አጋማሽ በኋላ ከሚጠናከሩ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች የተሻለ የደመና ሽፋን የሚኖራቸው ሲሆንና፣ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ ፡፡

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የጃንዋሪ ወር በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የሚኖረው የበጋው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ በመከናወን ላይ ለሚገኘው የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት ሰብልን ከማሳ የማንሳትና የማከማቸት እንዲሁም የመውቃት ተግባራትን በማከናወን ምርትን ከብክነት መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ከወሩ አጋማሽ በኋላ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በጥቂት የደቡብ ምዕራብ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምስራቅና የመካከለኛዉ ኪስ ቦታዎች ላይ የሚጠበቀው መጠነኛ እርጥበት ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞ የበልግ እርሻን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የአፈር ውስጥ እርጥበትን የሚያሻሽል እንዲሁም የማሳ ዝግጅትን አስቀድሞ ለማከናወን ጠቀሜታ የሚኖረው ሲሆን በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለሚገኙ የአርብቶ አደር አካባቢዎች የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦትን በመጠኑ እንደሚያሻሽል ይጠበቃል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የጃንዋሪ ወር አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር የሚቆዩ ሲሆን ይህም ሁኔታ በተለይም ከሚኖረው የቀኑ ትነት ጋር ተዳምሮ በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ የውሃ ማጠራቀምያዎች ማለትም በግድቦች፣ በወንዞች፣ በኩሬዎች እና በምንጮች



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ላይ የውኃ መጠን መቀነስ ሊያስከትል ስለሚችል የሚገኘውን የውኃ ሀብት በአግባቡ እና ለብክነት በማያጋልጥ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ይመከራሉ፡፡ በተጨማሪም ኦሞ ጊቤ፣ ገናሌ ዳዋ እና ስምጥ ሸለቆ በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ መጠነኛ እርጥበት የሚያገኙ ሲሆን መጠነኛ የእርጥበት መሻሻል እንዲኖር ያስችላል።



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et